መስከረም ፬ሺ.ህ ፫

# እምዬ ምኒልክ ላይ ለማጥላት ! ?

ከኮማንደር አሰፋ ሰይፉ

የተከበሩ ሼህ ሞሀመድ አል አሙዲ፡-በአንድ ዕውነትኛ ቁም ነገር ልጀምርልዎ። በቀኃሥ ዘመነ መንግሥት የኢየሩሳሌም ማኅበር እንደተጀመረ ምዕመናን በዘመኑ አይሮፕላናችን ዳኮታ ፫ (ያስታውሱት የል?) ለጸሎት መብረር ላይ እያሉ ኃይለኛ ሞገድ ተንስቶ ያችን አይሮፕላን ሲያናውጣት፡- ተንገላትታ ያንገላታቻቸው ተሳፋሪዎቿ ላይ ያሉት ምዕመናን ዓይተው የማያውቁት ገጠመኙ እጅግ አስፈራቸው። ኹሉም ጭንቀት ላይ ኾነው የሚይዙት የሚጥሉት ሲያጡ አንዷት እናት ብቻ (ወይ አስካለ ጋረደው) በተረጋጋ መንፈስ ዝም ብለው ዳዊታቸውን ይደጋማሉ። ቀልባቸው መለስ ያለላቸው ምዕመን ኹሉንም አይተው ዓይናቸው ወይ. አስካለ ላይ ሲያርፍ እንደተገለጸው ኾነው አግኝተዋቸው ርሳቸው ሲርበደበዱ አንዷት ደካማ አሮጊት በእንደዚያ ኹናቴ በመገኘታቸው ሀፍረትና ንዴት በተቀላቀለበት ድምጸት ከፍ ባለ ድምጽም።

> “ እሜቴ! ማለቃችን እኮ ነው!። ታድያ ርስዎ ዝም ማለትዎ እንዲህስ መኾንዎ ምንድን ነው?” ቢሏቸው የእሜቴ መልስ ሙሉ እምነት በተመላበት አነጋገር፡
> “ወደ ርሱ እየሄድን? አያደርገውም!!” ነበር። “ደግሞስ!’ አሉ ሲቀጥሉ፡- ‘ከመርበድበዱ መጸለዩ አይሻልም?”

እኔም ከአፄ ምኒልክ ሀውልት ወደደጎል አደባባይ ከሚወስደው መንገድ በስተቀኝ ያለው ክፍት ቦታ ላይ ትልቅ ሕንጻ ለመሥራት መግዛትዎን ስሰማ “የኢትዮጵያ አምላክ አያደርገውም” ነበር ያልሁት፡- ለራሴ! ምንም እንደእሜቴ እምነተ - ጠንካራ ባልኾንም። እስካሁን አቆይቶልኛል።

ለምን? ወዳልኩት ከመሄዴ በፊት ዘመኑ ረጅም ስለኾነ ለወጣቱ ስለዚያ ቦታ ትንሽ ልበል። እዚያ ቦታ ላይ ከአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ የተሠሩ ብዙ ቤቶች ነበሩበት። አንዳዶቹ በድንጋይ፡- አንዳንዶቹ በእንጨት ብዙዎቹ እንደማንኛውም ያገራችን ቤቶች ነበሩ። “ችምችም ያለው መንደር” የሚለው የተሻለ ሊገልጸው ይችላል። እነዚህም፡- ለመደብርነት፡- ለቡና ቤትነት ውስጥ-ውስጡም ለጉልትነት ኹል-ገብ ግልጋሎት የነበረው ነበር። ይኽን ችምችም ያለ መንደር ያነሱት (ያስፈራረሱት) ቢትወደድ ዘውዴ ገብረሕይወት ከንቲባ በነበሩበትና አዲሱን ማዘጋጃ ቤት ካሠሩ በኋላ ነበር። ለአዲስ

አበባ መልካም ገጽታን ለማትረፍ ብቻ ሳይኾን፦ አዲስ አበባ ውስጥ ለሕዝብ መዝናኚያ የሚኾኑ ብዙ ሥፍራዎች ባለመኖራቸውና አዲስ አበባም የአፍሪካ መዲና መኾኗ ሲጨመር ለእንደዚህ ዓይነቱ ክብር ተስማሚ ኹናቴዎችን ለማመቻቸት ነበር። ከቤት/ቦታዎች ባለቤቶች አንድ ኹለቱ ለዚህ የተቀድሰ ተግባር ግምትም ንጣፍም አንፈልግም ማለታቸውን ነግረውኛል። የሕዝብ መዝናኛዎችን ካነሳን ከደብረ-ጽጌ ሌላ በጉለሌ መንገድ የል.ራስ ኃይሉ ቤት እንደታለፈ ከድልድዩ በፊት ወደቀኝ በሚያስገባ መንገድ የሕዝብ መዝናኚያ ተከልሎ ነበር።

ይኽን ያራዳውን በተመለከተ ቢትወደድ ዘውዴ ያደረጉትን አንድ ያልተለመደ ነገር ላውጋዎ። አዲስ አበባ አራዳ ውስጥ በሬዎችን አስጠምደው አሳርሰውም ጤፍ ዘሩ። ምነው ቢባሉ “ የኢትዮጵያ ሕዝብ እህል ያከብራል። ስለዚህ አይጸዳዳበትም!” ማለታቸውን ስምቻለሁ። አኹንስ? ከመጸዳጃነት ድኖ ይኾን?
ሕዝቡስ ይህን ችግሩን የሚያቃልልበት ተሠርቶለት ይኾን?

ሼኩ፦ (ከዚህ ቀደም ሚያዝያ ፩ ቀን ፪ሺህ ፩ በጻፍሁት ተፈቅዶልኛል ብዬ ነው) ዓለምን የዞሩና ታሪካዊ ቦታዎችንም የሚያውቁ እንደመኾንዎ በየመናገሻ ከተሞች ውስጥ በሚገኙት ልዩ የአገር ባለውለታዎች ሀውልቶች አካባቢዎች ለተወሰነ ርቀት ሀውልቱን የሚቀብር ነገር አይሠራም። ለምሳሌ፦ በዋሽንግተን፦ የዋሽንግተን/ናሽናል፦ በለንደን ትራፋልገር ስኰር የኔልሰን፣- በፓሪስ አርክ ደ ትሪዮምፍ…

እነዚህ ኹሉ ሀውልቶች የተሠሩት ለዚያች አገር ለዋሉት ጀግኖች መታሰቢያ ነው። የእምዬ ምኒልክ እኮ ውለታ ለአንዲት ኢትዮጵያችን ብቻ አይደለም። በተለምዶ እንደሚባለውም “ለጥቁሮች ነፃነት” ም ፈር ቀዳጅነቱ ብቻ አይደለም። በዚያን ወቅት በነጮች ለሚበዘበዙት ኹሉ እንጂ። ከአፍሪካ ወጥተው ወደ አሜሪካ ቢሄዱ ወደ እስያ ወደ አረብም ቢመለከቱ የነጭ ተገዥዎች ነበሩ። በዚያን ወቅት “ነጭ የሚታየው በአይደፈሬነት! ነበር” እምዬ ምኒልክ ግን መላ አገራቸውን አስተባብረው ለአንደዬና ለመጨረሻ ጊዜ የነጭን ቆብ ቀደዱ፦የማይደፈር አለመኾኑን በማሳየት በቅን-ገዥዎች ሥር ለሚቃትቱት ኹሉ የነፃነትን ችቦ አቀጣጠሉላቸው። ውሎ-አድሮም ነፃ ኾኑ ( የፖለቲካ)

ስለዚህ፡ ሼኩ፦ አዎን ስለዚህ፦ ይህን ሀውልት የሚቀብር ሕንጻ ቢሠሩ የወገንን ክብርና ፍቅር የሚጨምሩ ከመሰለዎ ምናለ! ክብሬን ተዳፈረ የሚል ቁጭት ቀብሮ እንደሚያዩት ኧኸ.ኸ..! እያለ ቀን የሚጠብቅ ከኾነ ግን “ ለየትኛው ዓለም?” እዚህ ላይ ሳላነሳው ብቀር

ራሴን ለጸጸት ስለምዳርግ፦ ምናልባት ርስዎም ይኸንኑ በመገንዘብ ይኾን ይኾናል እስካኹን የአንዳንድ ጋዜጦችንና ባለሥልጣኖችን አፍ ችለው ያደቡት። ይህ ከኾነ “ ይባርክዎ”

የእኔ ምኞት ለአፍሪካ መሪዎች ምቹ ሆቴል መሥራት ላይ እንደመኾንዎ ለኢትዮጵያና ለአፍሪካ እንዲሁም ለሰው ልጅ ነፃነት ክብርና ፍቅር ላላቸው ኹሉ መታሰቢያ ይኾን ዘንድ እጹብ ድንቅ የኾነ ወደር የሌለው መናፈሻ እምዬ ምኒልክ ሀውልት አጠገብ ቢያሠሩ ለራስዎ ሀውልት እንደተከሉ ይቆጠራል። የቀድሞዎቹ ያቀዱትን መፈጸምዎም ያስከብሮታል።

ከሥሩ ግን የመኪና ማቆሚያዎችንና ለነብኺዎች የሚኾኑ መደብሮችንና ቡና ቤቶችን እንዲሁም መጸዳጃዎችን ቢያዘጋጁ “ ዝበለጸ!” ይባል ይመስለኛል። ይኸን፦ የገዙበትን፦ ካላደረጉ ቢባሉ፦ የሕዝቡን ጥላቻ ቀንበር ከጫንቃዎችዎ ወደሚሉዎት ወርውረው ቢገላገሉ ጥቅሙ እንጂ ጉዳቱ ጊዜያዊ ብቻ የሚኾን ይመስልኛል። ባጭሩ ‘የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ፦ ታሪክህን አክብሬ ላስከብርልህ ሞክሬ ነበር። ውርድ ከራሴ!” እንደማለት ይቆጠርልዎታል።

# ሠራተኞችን ከውጪ ስለማስመጣት

ቻይናዎች ለማንኛውም ሥራቸው ወገኖቻቸውን እንደሚያስመጡ ተረድተናል። የነሱን በታላቅ ሃዘን ልለፍና ኢትዮጵያዊ ወደኾኑት ወደርስዎ ልመለስ። “በጨለማ ቢያፈጡ - በባዳ ቢቆጡ” እንደሚባለው ስለኾነ።
ሠራተኛን ከውጪ ለማስመጣት የሚሰጠው ሰበብም ኾነ ምክንያት ኢትዮጵያዊው ሠራተኛ “ሰነፍ ስለኾነ ነው” ነው። እንዲያውስ “ ሥራ የማይወድድ፦ እንደአሳማ የሚራባ! “ ተብሎ ተሞግሶ የለ? ሕዝብን - ያውም የኢትዮጵያን ሕዝብ እንዲህ ይሉታል? ምን ነበር የሚባለው? ልለፈው። (ቀለል ያለው) አምስት ደቂቃ ሠርቶ አሥር ደቂቃ ያርፋል ይባላል። ከኾነ ለምን? የውጪው “ ሰነፍ” ይበለው/ን ርስዎማ እንዴት አርገው? ወገንዎን እያወቁ? አንዲት ስንኝ ላካፍልዎ፦

“ለምን ታሚዋለሽ አንቺም እንደሌላ
የት አንጀት ይበላል እሹቴ ቀጸላ?”

እሸቴ ቀጸላ የሚባል ወዳጅዋ ሞቶባት "አንጀቴን በላኸው" እያለች ስታለቅስ እህትዬዋ የመለሰችላት ነው። ቅኔውን እንኳን ለሌላ እንደሚተርፉ እሰማለሁ። ቢኾንም - የማያውቅ አለ አይደል?

መሬቱን ተነጥቆ፡ ሥራ አጥቶ ከችግሩና ከችጋሩ የተነሳ ቆዳው አጥንቱ ላይ የተጣበቀ መኾኑን እያዩት? በዚህ ላይ ወባው፦ የዓባለ-ዘር በሽታዎች፦ ጫቱና ዕፀዋቱ.. በየዓይነቱ... ስንቱ እየተረባረበበት!? እየሳለ ትንፋሹን ለመመለስ ዐቅም የሚያንሰው መኖሩን አይሰሙ ይኾን? ታዲያ ይሄ ምስኪን በምን ዐቅሙ ይሥራ? በነፍስም በስጋም የሚጠቅመው እንደዚህ መላ ለጠፋው፦ ግራ ለገባው ወገን መላ መምታት አይሻልም? "አይዞህ አለሁልህ" ማለትስ አይጠቅምም? ርግጥ ነው በዓለም ላይ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ድርጅቶች እንዲሚነግሩን ከ፱-፲፬ ሚሊዮን የሚኾኑ ወገኖቻችንን ኹሉ ከችጋር ይገላግሉ ለማለት አልደፍርም። ግዳጅዎ ነው ብዬም አላምንም። በአንጻሩም ሲያባብሱበት ዝምብሎ ማየቱን ኅሊናዬ አይቀበለውም። በሕግም አንድ ሰው ውሀ ሲወስደው እያዩ ዝም ማለት ከነፍሰ ገዳይነት እንደሚያስቆጥር ዕውን ነው። ሲኾን ሊያድነው ቢችል አልያም ቢሞክር ሰብአዊ ግዴታውን እንደተወጣ ይቆጠርለታል።እኔ ግዳጄን ልወጣ። የርስዎንና የገዥዎችን ለእናንተው ልተው።

ችግሩን አውርቶ መተው "አልኩ!" ባይነት ነውና መፍትሄ (ዎች) የሚመስሉኝንም ላካፍልዎ።

ሀ- ልዩ ባለሞያዎች፡-

አገራችን ውስጥ ብዙ የሚፈልጓቸው ዓይነት ባለሞያዎች እንደማይኖሩ፡ ጥርጥር የለውም። ታዲያ ኹለዬም በውጪዎቹ ከመተማመን የራስን ማሠልጠን አይጠቅምም? ማለቴ፦የሚፈልጓቸው ዓይነት ዕውቀት ካሏቸው ለመምሕርነት የሚያስፈልጉትን አስመጥተው የሚፈልጉትን ያህል ሰው ቢያሠለጥኑ እነዚህን ወገኖችዎን የዕድሜ ልክ እንጀራ ከፈቱላቸው ማለት ነው። አያጸድቅም?

ለ- የጉልበት ሠራተኞች፦

እነዚህን ልጆችዎ የሚኾኑትን ሥጋቸው ከአጥንታቸው ተጣብቆ የሐቴል ቤት ትራፍራፊን በምጽዋት ካገኙት ለአንድ ጉርሻ ፪-፫ ብር እየከፈሉ የሥቃይ ዘመናቸውን ለማራዘም በጫቱና በመሰሉት ለመግፋት የሚጥሩትን ሰብሰበው ለኹለት-ሦስት ወራት የሰው ልጅ (ድሀው) በልቶ የሚያድረውን/እንደችሮታዎ ቢቀልቧቸው በባለውለታነት የሚፈልጉትን ይሠሩሎታል። ሊያገኙ የሚችሉት የመንፈስ ርካታ የመጀመሪያዎን ቢሊዮን ካገኙበት ሳይበልጥ

ይቀራል? ራሱን ከልመና ውርደት ከማዳን አልፎ እንደባህሉ መርዳት የሚገባውን ለመርዳት ሲችል ርካታው ለርስዎ ከላይ ከተጠቀሰው ርካታ የሚያንስ አይመስለኝም። በዚህ ተግባርዎም የአምላክዎን ቆጠራ ለርሱ ትቼ በቀጥታ ከተጠቀሙትና ከሚጠቀሙት (ከርስዎም በኋላ ሊቀጠሩ ስለሚችሉ) ውለታዎ በምድርም ከፍ ያለ ይኾናል። የወጪን ነገር ለመዝጋት፤- ለ፳ሺህ ሠራተኛ የደርሶ መልስ ወጪና የምንዛሪ ነገር ሲነሳ መልሱ ምን እንደኾን ለርስዎው ልተወው።

ሐ- በተጨማሪ ሊታዩ የሚገባቸው፡-( እንደማምንበት)

፩- እነዚህ ከውጪ የሚመጡት ፳ሺህ ፳፪ ጎረምሶች በልተው ጠጥተው የሚያስፈልጋቸውን ሲፈጽሙ ከሚያስከትሏቸው ውስጥ

- የአባለ-ዘር በሽታዎች
- ዲቃሎች

ሕክምናን በተመለከተ አገራችን ውስጥ ያለውን ስለሚያውቁት እንዲያው በደፈናው ተቀጣጥሎ ማለቅ-መሰቃይት አይኾንም? የሀገሪቱ የዚህ ጉዳይ አላፊዎች ቢገቡበት መልካም ነበር።
የዲቃሎች ነገር ሲነሳ፡- አገራችን ውስጥ ከሚወለዱት በሕጻንነታቸው የሚቀጩት ስንትያዎች (ከመቶ) ናቸው? ቤት ይቁጠረው።ከዚህ የተረፉትንስ አገሪቱ ማሳደግ እያቃጣት በጉዲፈቻ ወደ ውጪ የሚነገድባቸው በመቶ ሺዎች መቆጠራቸውን አላነበቡ ይኾን? ተጽፏል።
እንግዲህ፡- "…ያደርሳል እንጂ…" እንደሚባለው አድርሻለሁ። ዓይነ-ልቦናዎን አብርቶልዎት አገር-ወገንን የሚጠቅም እንጂ የሚጎዳ ተግባር እንድይፈጽሙ ይርዳዎ።

ሚያዝያ ፩ ቀን ፪ሺህ ፩ የጻፍሁሎትን በሀዘን እያስተወስሁ፡- በመጨረሻው ረድፍ ላይ ያለውን እንዲያተኩሩበት በድጋሚ አደራ እላልሁ።
ለመዝጊያ ቢትወደድ ዘውዴ የአገር አስተዳደር ሚኒስትር በነበሩበት ወቅት ኢዲ አሚን አንድ በዐሉን (የጋብቻ?) ሲያከብር ልዑካንን መርተው ያዩት እጅግ አስገርሚቸው ያሉት ትዝ አለኝ።

ለካምፓላ ብቻ ይኹን ለመላ ዩጋንዳ ትዝ አላለኝም። የማስታውሰው ለሦስት ቀናት ያህል ነጻ ቢራ ተፈቅዶላቸው ሰዉ ኹሉ ሲንዟባረር አይተው ፡-" እዚህ አገር ተማሪ የለም እንዴ?" ማለታቸውን ነው።

**የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ!**